የሰበር መ/ቁ 154802

ሐምሌ 19 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- 1. አቶ ድንበሩ ፈቃደ

2. ወ/ሮ ሙናዬ ሁሴን ቀረቡ።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ እታለም እውነቴ - ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

# ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሁኑ 1ኛ አመልካችና በአሁኗ 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍፍል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በደላንታ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት በአሁኑ 1ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው።የአሁኗ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ሌላኛዋ ሚስት ሲሆኑ በወረዳው ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ተከራካሪ የነበሩ ናቸው።

ግራ ቀኙ ሲከራከሩባቸው በቆዩት የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይኼው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለንጢት ከተባለ ሰፍራና አደገ ከተባ ሰፍራ ያሉትን ቤቶች በተመለከተ የአሁኑ 2ኛ አመልካችና ተጠሪ ከአሁኑ 1ኛ አመልካች ጋር በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተፈሩ መሆናቸው ተረጋግጦአል በሚል ድምዳሜ ንብረቶቹን በአይነት እኩል እንዲካፈሉ፣ በአይነት እኩል መካፈል የማይቻል ከሆነም ተሸጦ ገንዘቡን እንደየድርሻቸው ይካፈሉ፣ ሠየአሁኑ 1ኛ አመልካች ለተጠሪ ከፈልኩ የሚሉትን ብር 30,000.00 በተመለከተም ለተጠሪ አባት እንጂ ለተጠሪ ያልተከፈላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ 1ኛ አመልካች የተጠሪን አባት የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው፣ የአሁኑ 1ኛ አመልካካች ለንግድ ስራ በኪሉ ያለውን ገብር 150,000.00 ሶሰቱም እኩል እንዲካፈሉ በማለት በሌሎች ነጥቦች ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል።፣

ከዚህ በኋላ የአሁኑ አመልካቾች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ቸሎት አቅርበው ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከተደረገ በኋላ ይኼው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል። በአመልካቾች በኩል የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ አሻሽሎ ብር 150,000.00 ላይ የተሠጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ ሽሮ ወደ ታች ፍርድ ቤት ተመልሶ እንዲጣራ በማለት ሲወስን በሌሎች ንብረቶች ላይ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን አጽንቶታል።

አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም በዚህ ምክንያት ሲሆን የሰበር አቤቱታቸው መሰረታዊ ይዘትም 1ኛ አመልካችና ተጠሪ ባልና ሚስት ናቸው ተብሎ መወሰኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አዳገ በተባለ ቦታ ላይ ያለውን

ቤት ሶስቱም እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ መወሰኑ 1ኛ አመልካችና ተጠሪ በ12/06/2007 ዓ.ም የአደረጉትን የጋብቻ ውል ይዘት ያላገናዘበ ነው በሚል በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ውሳኔ እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው። አቤቱታቸው አዳጎ በተባለ ቦታ ያለውን ቤት በተመለከተ 1ኛ አመልካች ከተጠሪ ጋር በቀን 12/06/2007 ዓ/ም አደረጉ በተባለው የጋብቻ ውል ላይ የጋራ ብለው ባላመለከቱበት ሁኔ ተጠሪ በዚህ ቤት ላይ 1/3ኛ እንዲያገኙ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተጠሪ ሲሆን ተጠሪ በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ የጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱተው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል።

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የተቻለው 1ኛ አመልካችና ተጠሪ ከየካቲት 15 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 16 ቀን 2008 ዓ/ም ድረስ በጋብቻ ውስጥ የነበሩ መሆኑን፣ የአሁኑ አመልካቾች ደግሞ ከ2002 ዓ/ም ጀምሮ እስከሁን በጋብቻ ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፣ ለንጤት በተባለ ቦታ የሚገኘውን ቤት በተመለከተ በ2005 ዓ/ም በፍርድ ቤት ሐራጅ ሽያጭ 1ኛ አመልካች ከአቶ ሃይሌ ሞላ ጋር ታርቀው የተረከቡትና ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተፈራ ሁኖ ከ2ኛ አመልካችና ከተጠሪ መካከል ለንብረቱ መፈራት የተለዬ አስተዋጽኦ ያደረገ ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ያለመቅረቡን፣ አደጎ በተባለ ቦታ ያለውን ቤት በተመለከተ ከአቶ ታረቀ ዘውድነህ በ12/02/2007 ዓ/ም የተገዛ መሆኑና 1ኛ አመልካች ይህን ንብረት በተመለከተ የግሌ ነው የሚሉትን ምክንያት ዘረዝረው ክርክር ያላቀረቡበት ጉዳይ መሆኑን፣ 2ኛ አመልካች ቤቱን ብር 300,000.00 አውጥተው ያደሱት ስለመሆኑ ገልጸው የተከራከሩ ቢሆንም በማስረጃዎቻቸው ይህንኑ ያላስረዱ መሆኑንና ለዚህ ቤት መፈራትም ከሁለቱ ሚስቶች የተለዬ አስተዋፅኦ የአደረገች ስለመኖሯ በማስረጃ ያለመረጋገጡን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ አስፍሮ እነዚህ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ለሶስት እኩል እንዲካፈሉ የወሰነ መሆኑን፣ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን ረገድ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር ተመሳሳይ ስልጣን ያለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህንኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቤቶቹ የሶስቱም ተከራካሪዎች ንብረቶች ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትን የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሙሉ በሙሉ ያፀና መሆኑን ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ከ1ኛ አመልካች በጋብቻ ውስጥ የነበሩት ጊዜ ከመቼ እስከመቼ እንደሆነ፣ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት መኖር ያለመኖሩና በጋብቻ ጊዜ በተፈራው ንብረት ላይ ከሁለቱ ሚስቶች የተለዬ አስተዋፅኦ ያደረገችው የትኛዋ ናት? የሚሉት ነጥቦች ፍሬ ነገሩን ማጣራትንና ማስረጃን መመዘንን የሚጠይቁ በመሆናቸው ይኼው ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በሕጉ አግባብ ፍሬ ነገሩን አጣርተውና የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መዝነው ተገቢ ነው ያሉትን ድምዳሜ መያዛቸውን ነው። ይህ ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም። ምክንያቱም ለዚህ ችሎት በሕግ ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ወይም የማስረጃ ምዘናን ማቃናት አለመሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነውና። በመሆኑም አከራካሪ የሆኑ ንብረቶች የግራ ቀኙ ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉም ተመሳሳይ አስተዋፅኦ አድርገዋል ብሎ ግምት መውሰድ በሚቻልበት ሁኔታ የተፈሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ከሆነ 1ኛ አመልካችና ተጠሪ በ12/06/2007 ዓ/ም አደረጉ በተባለ የጋብቻ ውል አዳጎ በተባለ ቦታ ያለውን ቤት በተመለከተ በሰነዱ ላይ ሳይገለጽ መታለፉ በክፍፍሉ ላይ የሚያስከትለው የተለየየ ሕጋዊ ውጤት የለም።

ወደ ሕጉ ስንመጣም አንድ ወንድ በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሴቶች ጋር ጋብቻ ፈጽሞ የሚኖርበት ሁኔታ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ ዕውቅና ያልተሰጠው በመሆኑ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ አንደኛው ወይም ሁለቱም ጋብቻዎች ፈርሰው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በሚነሳበት ወቅት ጉዳዩ አልባት ማግኘት የሚገባው የክፍፍል ጥያቄው ክርክር ባስነሳው ንብረት መፈራት ወይም መገኘት ውስጥ እያንዳንዱ ተጋቢ ያደረገውን አስተዋጽኦ እና ንብረቱ የተፈራበትን ጊዜ ሁለቱ ጋብቻዎች ከተቋቋሙበት ጊዜ አንጻር በማገናዘብ መሆን ይገባዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 45548፣ 50489 እና በሌሎችም በርካታ መዝገቦች በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ይህ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ደግሞ በሕጉ አግባብ እስካልተቀየረ ድረስ ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተፈጻሚ ሊደረግ የሚገባው ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት እንዲታይ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ጭብጥ ተለይቶ የተያዘበትና አከራካሪ የሆነው፤አዳኅ በተባለ ቦታ ላይ ያለውን ቤት የግራ ቀኙ ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ የተፈራና ከሁለቱም ሚስቶች መካከል የተለዬ አስተዋጽኦ ያደረገች ስለአለመኖሯ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ሶስቱም እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በጋብቻ ጊዜና በንብረት ክፍፍል ጊዜ ተጋቢዎች እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ የሚደነግገውን የህገ መንግስቱን ድንጋጌን እንዲሁም በቤተሰብ ሕጉ ስለንብረት ክፍፍል የተቀመጡትን መርሆዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አዳኅ በተባለ ቦታ ያለውን ቤት በተመለከተ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 26878 በ14/02/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-04711 በ26/08/2009 ዓ/ም፣ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-18384 በ08/06/2010 ዓ/ም የጸናው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ጸንቶአል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ብር 150,000.00 አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ እና በሌሎች ንብረቶች ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሠጡት ውሳኔ በዚህ ችሎት አልተነኩም፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትእዛዝ

በ30/06/2010 ዓ/ም ተሠጥቶ የነበረው እግድ ተነስቶአል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**